## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢ.ጋን)

ሚያዚያ 1፣ 2004ዓም

# ጋምቤላ ተጨንቃለች!!

# “በመሬታችሁ ላይ ሙቱ፤ በመሬታችን ላይ እንሙት”

ጋምቤላን የሃዘን ጽልመት አልብሷት በነበረው የታዳጊ ወጣት የቀብር ስነ ስርዓት ላይ ሽማግሌዎች ይንን ተናገሩ “. . . **የጉዳታችንን መጠን እናውቀዋለን። የሃዘናችንም ጥልቀት እናስተውለዋለን፡፡ . . . በመሬታችሁ ላይ ሙቱ፤ በመሬታችን ላይ እንሙት፤ ሁላችንም እናልቃለን እንጂ መሬታችንን ለቀን ወዴትም አንሄድም፤ አትፍሩ፤ መንፈስ ጠንካራ ሁኑ፤ የበቀል መልዕክተኛ አትሁኑ፤ ለፍትህ ግን ቁሙ። ረዳት እንደሌለን አንሁን። ልጃችን የሰላም እረፍት ላይ ነው . . .”** ፍትህ የተጠሙ ልቦች አነቡ። በደል የሌለበት የ18 ዓመት ታዳጊ በጥይት ተገደለ። በሺህዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች በአንድነት እምባቸውን ወደ ሰማይ እያመለከቱ በመራጨት ሃዘናቸውን በቁጣ ገለፁ - የፍትህ ያለህ እያሉ።

ይህ የሆነው ከትላንት በስቲያ ቅዳሜ መጋቢት 29 ቀን 2004 ዓም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት አካባቢ በህወሃት/ኢህአዴግ ነፍጥ አንጋች የመከላከያ ወታደሮች በጥይት ተደብድቦ ህይወቱ ያለፈው **የጋምቤላ ታዳጊ ወጣት ቲዶ ኩል ኡማን የቀብር ስርዓት በተፈጸመበት ወቅት ነው፡፡ ታዳጊ ቲዶ ኩል ዕድሜው 18 ሲሆን የ12ኛ ክፍል ተማሪም ነበር፡፡**



ቲዶ ኩል በሚኖርበት ሰፈር ለተወለደ ህፃን በተዘጋጀ ስም የማውጣት ስነስርዓት ላይ ከተገኙት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። በባህሉና በቆየው የአካባቢው ልምድ መሠረት ነዋሪዎቹ ስነስርዓታቸውን እያከናወኑ ሳለ፣ አምስት የሚሆኑ ነፍጥ ያነገቱ የህወሃት/ኢ.ህዴግ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በድንገት ወደ ቦታው መጡ፡፡ ወደ ዝግጅቱ ግቢ ተጠግተው ቲዶ ኩልን ጠሩት። ሲቀጥሉም "መታወቂያህን አምጣ አሉት"፡፡ ታዳጊውም ተማሪ መሆኑን፣ በከተማዋ ነዋሪ መሆኑንና የሰራው ጥፋት ስለሌለ ለምን መታወቂያ እንደተጠየቀ እንዲያስረዱት ጠየቀ። ትዕዛዙና ድግሱ ቀደም ሲል ታዳጊውን መግደል በመሆኑ መታወቂያ እንዲያሳይ ወታደሮቹ በኃይለቃል አዘዙ።

ጥያቄው አግባብ ሆኖ ያልተሰማው ታዳጊ ወደ ክብረበዓሉ ተመልሶ እየሄደ ሳለ ከኋላው ጥይት ተለቀቀበት፤ በጀርባው የገባው ጥይት ደረቱን ጥሶ ሲወጣ በአፍጢሙ ተደፋ፤ በልቡም ተደፍቶ ደሙ እንደውሃ ፈሶ አለቀ። በቅፅበት ልዩነት የ18 ዓመቱ ወጣት ቲዶ ኩል ኡማን ተቀጠፈ። ነፍሰገዳዮቹም ጀርባቸውን አሳይተው፣ "ግባቸውን" አሳክተው ተመለሱ። የህፃን ስም ለማውጣት በተጠራ ክብረበዓል የተሰበሰቡ ባልጠበቁት ሁኔታ ደስታቸው ወደ ሐዘን ተቀየረ፤ በሲቃ ተላቀሱ፤ የተወለዱበትን ቀን ረገሙ፤ በምሬትም አወገዙ። ቀጥሎም በጉዳዩ ወደሚጠረጠር አንድ ነጋዴ መኖሪያ ቤት አመሩና ቤቱን እሳት ለቀቁበት፤ አጋዩት።

በስፍራው የነበሩ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የመረጃ ምንጮች የነጋዴው ቤት የተቃጠለበትን ምክንያት መመርመር ጀመሩ። እንደ መረጃ ሰዎቻችን ገለፃ ነጋዴው ሰው ረፋዱ ላይ ሟችን እያመለከቱ "ይህ ልጅ ጥጋበኛ ነው፤ ሽፍቶችን ይረዳል፤ የሽፍቶች አጋር ነው" በማለት ለህወሃት/ኢ.ህአዴግ መከላከያ አባላት ሲያሳብቁ የሰሙዋቸው ነበሩ። ነጋዴው የመከላከያ ወታደሮች ፊት ለፊት ቆመው ይህን በተናገሩ በአራት ሰዓታት ውስጥ ታዳጊው በጥይት ተበሳስቶ እንዲሞት ተደረገ። ይህንን የተረዱ፤ በታዳጊ ጓደኞቸውና ወገናቸው አሟሟት የተቃጠሉ በቀጥታ ወደ ነጋዴው ቤት በማምራት እሳት ለኩሰው ያነደዱት።

አንድ የክልሉ ፖሊስ አባል ለመከላከያ ካምፕ ስልክ በመደወል የነጋዴው መኖሪያ ቤት መቃጠሉን ሪፖርት ሲያደርጉ አራት መኪና ጦር ተወርውሮ በመምጣት በአካባቢው የነበሩ ወጣቶችና አዛውንቶችን ደበደቡ፤ አሰሩ። አንድ ተሽከርካሪ በርካታ ሰራዊትን በመያዝ የሟች አስከሬን እወደቀበት ግቢ አመራ። ይህ ሁሉ ሲሆን የሚከታተሉት የአኢጋን የመረጃ ሰዎች ከስፍራው እንደዘገቡት ፖሊስ አስከሬኑን ለመውስድ ሲሞክር ተቃውሞ ባሰሙት ላይ የመከላከያ ሰራዊት የወሰደው ርምጃ ህግና ህገ መንግስታዊ ዋስትና በጋምቤላ ዋጋ የሌላቸው መሆኑን የሚያመላክት እንደሆነ ይገልጻል።

ጃኬቱን በማውለቅ አስከሬኑን የሸፈነው አኛች የተባለ የሟች የክፍል ጓደኛ ፖሊስ አስከሬኑን ለመውሰድ ሲል "እኔንም ግደሉኝ። ሁላችንም ግደሉን። ወንድሜን አትወስዱም..." በማለት ሲናገር አብረውት የነበሩትም በህብረት ተቃውሟቸውን አስተጋቡ። በስፍራው የነበሩት ወታደሮች ሃይል በመጠቀም የቻሉትን ደበደቡ፤ አሰሩ። በመጀመሪያ ተቃውሞ ያሰማው አኛች ክፉኛ ተደብድቦ እስር ቤት እንዲገባ ተደርጓል። ይህንን ዘገባ እስካጠናከርንበት ጊዜ ድረስ ስለ መፈታቱም ይሆን ተጨማሪ ስለደረሰበት ጉዳት የቀረበ ሪፖርት የለም።

የመረጃ ሰዎቻችን ሪፖርት አስገራሚ እንደሆነ በመግለጽ ያሰፈረው ዜና የሟች አባትን ኩል ኡማንን የሚመለከት ነው። የታዳጊ ወጣት ቲዲኮል ኡማን አባት የዲማ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ናቸው። "የልጃቸውን መሞት ከሰሙ በታጠቁት መሳሪያ ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ጉዳት ያደርሳሉ" በሚል መሳሪያቸውን እንዲፈቱና እስር ቤት እንዲገቡ ተደርጓል። የልጃቸውን መገደል የሰሙትም እስር ቤት ከገቡ በኋላ በሚቀርቧቸው ሰዎች አማካይነት ነው። ስለ ፖሊስ አዛዡ የሚያውቁ እንደተናገሩት አባትና ሟች ልጃቸው የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና እጅግ የሚዋደዱ ነበሩ።

ይህ ከመፈጸሙ ሁለት ቀን በፊት በአቦቦ ወረዳ አኩና ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆነች ሴት ውሃ ቀድታ ስትመለስ የመከላከያ አባላት ያገኟትና "ባልሽ የት ነው?" በማለት ጥያቄ ያቀርቡላታል። እሷም ለጊዜው ባሏ የት እንደሄደ እንደማታውቅ ስትመልስ "እንዴት" በሚል ወታደሮቹ ይደበድቧታል። ምንም የምታውቀው ነገር እንደሌለ በተደጋጋሚ ብትገልፅም ሊያዳምጧት አልቻሉም። በመጨረሻም ዱላውን አቁመው በነደደ የእንጨት ፍም አቃጠሏት። የዓይን ምስክሮች እንዳስታወቁት ሴቲቱ ክፉኛ በመጎዳቷ አቦቦ ሆስፒታል ትገኛለች።

አቦቦ ወረዳ አማጺያን ያሉበት ጫካ የሚገኝ መሆኑን የፌደራል ደህንነት ካስታወቀ በኋላ የመከላከያ መኮንኖች፣ የክልሉ የፖሊስ ልዩ ሃይል አዛዦች፣ የክልሉ ፕሬዚዳንትና የደህንነት ሃላፊዎች፣ ህዝቡን በመሰብሰብ "ሽፍቶቹን አድናችሁ አምጡ" በማለት የማስፈራሪያ ትዕዛዝ በተደጋጋሚ ሰጥተዋል። ህዝቡም ትልቅ፣ ትንሽ፣ ሽማግሌ፣ ወጣት ሳይል በጠዋት "ሽፍታ አደን" ውለው ባዶ እጃቸውን ሲመለሱ "እንዴት ይጠፏችኋል" በማለት ከአርባ በላይ ሰዎችን አስረዋል።

የመረጃ ምንጮቻችን እንዳሉት ሽፍታ ለማደን ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ታዳጊ ህጻናት ሳይቀር በተከታታይ ቀናት ጠዋት ከቤታቸው በመውጣት ጫካ ውለው ባዶ እጃቸውን ሲመለሱ የሚደርስባቸው ዱላና ማስፈራሪያ ከገደቡ ያለፈ ሆኗል። አንድ በድርጊቱ የተበሳጩ አዛውንት **“እኙዋክ የሆንን ሁሉ በጅምላ ሽፍታ እየተባልን መከራ እያየን ነው”** ሲሉ ምሬታቸውን ገልፀዋል።

“ባልሽን ከላመጣሽ” በሚል ድብደባ በተፈፀመበት ቀን በቀበሌውና ባካባቢው ወረዳዎች የትምህርት ስራ በመቆሙ ሻንጣውን ይዞ ወደ ቤተሰቦቹ ለማምራት አውቶቡስ ፍለጋ በሚጓዝ መምህር ከኋላው በጥይት ተደብድቦ ህይወቱ አልፏል። ማንም ጠያቂ የሌላቸውና በክልሉ ተወላጆች እየተመሩ እንደ አውሬ ግድያ የሚፈጽሙት የህወሃት/ኢህአዴግ ሰራዊት በካራቱሪና በሼክ መሃመድ ሁሴን አላሙዲ እርሻ አካባቢ ነዋሪዎች ላይ እየፈጸሙት ያለው ግፍና ወንጀል የክልሉን ሰላምና ጸጥታ አደጋ ውስጥ በጣለበት ወቅት የኑዌር ብሄረሰብ አባላትን ያስቆጣ ግድያም ተከናውኗል።

ከሁለት ሳምንት በፊት በኢታንግ ወረዳ የኑዌር ብሄረሰብ አባል በሆነ የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት መምህር በመከላከያ አባላት በጥይት መገደሉ የጋምቤላን ሰላም ይበልጥ ያናጋ ሆኗል። መላው የኑዌር አባላት መሳሪያ የታጠቁ፣ ትጥቃቸውን ይዘው በግልፅ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸውና ግድያውን ተከትሎ ለክልሉና ለፌደራል ባለስልጣናት ያቀረቡት ጥያቄ ምላሽ አለማግኘቱ ተመጣጣኝ በቀል ይወስዳሉ የሚል ስጋት ፈጥሯል።

እንደ መረጃ ሰዎቻችን ዘገባ የኑዌር ብሄር አባላት መምህሩን የገደለው የመከላከያ አባል ለፍርድ እንዲቀርብ፣ ዓይናቸው እያየ እርምጃ እንዲወሰድበት ጠይቀዋል። በዚሁ መነሻ መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ.ም “መምህሩን የገደለው የመከላከያ አባል ተገድሏል” በማለት የክልሉ መሪና የህወሃት/ኢህአዴግ ሰራዊት መኮንኖች ህዝብ ሰብስበው መግለጫ ቢሰጡም የገጠማቸው ምላሽ አንገት የሚያስደፋ ነበር።

“እናንተን አናምንም። አንፈልጋችሁም። የሞተውን ወታደር አስከሬን ማየት እንፈልጋለን አምጡልን” በማለት የተሚገቱት የኑዌር ብሄረሰብ አባላት ተመጣጣኝ የሚሉት እርምጃ በገዳዩ ወታደር ላይ አይናቸው እያየ እንዲወሰድ ያቀረቡት ጥያቄ መመለስ ስላለበት “ማን የወታደር ልብስ ለብሶ ይሰዋል” የሚለው ጉዳይ አነጋጋሪ ሆኗል።

መጋቢት 30 ቀን 2004 ዓ ም እድሜያቸው ከ14-16 የሚሆን አራት ታዳጊዎች ከወንዝ ሲመጡ የደረሰባቸውን በመዘርዘር ሪፖርታቸውን ያጠቃለሉት የአኢጋን የመረጃ ሰዎች እንደገለጹት ታዳጊዎቹ ከወንዝ ሲመጡ “ሽፍታ ትረዳላችሁ፤ ጫካ ካሉት ሽፍቶች ጋር ግንኙነት አላችሁ” በሚል የመከላከያ አባለት ክፉኛ ቀጥቅጠዋቸዋል። ዱላው የጎዳቸው ለዓቅመአዳም ያልደረሱ ታዳጊ ህፃናት በአሁኑ ጊዜ ፉኚዶ ሆስፒታል ይገኛሉ። ሪፖርቱ አስከተጠናቀረበት ድረስ ታዳጊ ህፃናቱ የሚገኙበት ሁኔታ አልታወቀም።

“መሬታቸውን እየተነጠቁ የሚፈናቀሉት፣ በየቀኑ የሚገደሉት፣ በተለያዩ እስር ቤቶች ድብደባና አሰቃቂ በደል የሚፈፀምባቸው፣ ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት በጅምላ የተጨፈጨፉ ወገኖች በአደባባይ ፍትህ ያገኛሉ። ዓለምና እውነት የሚያስተምሩን ይህንኑ ነው። ከዛሬ ስድሳ ዓመት በፊት የሰዎችን ዘር በደምና በዘር ለይተው የጨፈጨፉ ፍትህ አደባባይ ወጥተዋል” በማለት በመላው አገራችን ፍትህ እንዲሰፍን ባላሰለሰ እንደሚሰራ ያስታወቀው የጋራ ንቅናቄያችን፣ **በመላዋ ኢትዮጵያ እንዲሁም በጋምቤላ እየተወሳሰበ ለመጣው ችግር የአቶ መለስ አገዛዝና አቶ መለስን በቀጥታ ተጠያቂ ያደርጋል።** ከዋናው መሪ ጀምሮ በተዋረድ እስከ ክልልና መከላከያ ሠራዊት ድረስ የሚገኙ ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ፍትህ ወዳድ ሃይሎች ጋር እንደሚሰራ አስታውቋል። በዚህ ሂደት ውስጥ **“እኔ ትዕዛዝ ፈጻሚ ነኝ፤ ተጠያቂዎቹ አዛዦቼ ናቸው”** ማለት ፍትህን ለማስበየን ከሚደረገው ተግባር የማምለጫ ምክንያት ተደርጎ ሊቀርብ እንደማይችል የጋራ ንቅናቄያችን በጥብቅ አሳስቧል፡፡

ማንም ትዕዛዝ ይስጥ፣ ማንም ይፈፅመው በጋምቤላ ንፁሃንን እየገደሉና እያሰቃዩ ያሉ እያንዳንዳቸው በፍትህ አደባባይ የዘሩትን እንደሚሰበስቡ ያስታወቀው የጋራ ንቅናቄያችን “የትኛውም አገዛዝ የዘላለም እድሜ የለውምና ፍትህ በኢትዮጵያ ይሆናል። ወገኖቻችንን እያስገደላችሁና የአገራችሁን ሃብት በማዘረፍ ተባባሪ የሆናችሁ ከወዲሁ ራሳችሁን አግልሉ” የሚል ጥሪም አስተላልፏል።

**የአንዱ በደል የሁሉም በደል መሆኑን በጥብቅ በሚያምነው በጋራ ንቅናቄያችን አመለካከት መሠረት በአሁኑ ጊዜ ያጣነው ወጣት ቲዶን ብቻ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያችን በየቀኑ አያሌ ቲዶ ኩሎች በህወሃት/ኢህአዴግ ይቀጠፋሉ፡፡ ቲዶን በስሙ ስለምናውቀው በስሙ እንጠራዋለን፤ ነገር ግን በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ ወዘተ እጅግ በርካታ ስምየለሽ ቲዶ ኩሎች**

**ደማቸው ይፈሳል፡፡ የኢትዮጵያ እናቶችም ከመሃል አገር፣ ከታች አገር፣ ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ፣ ከምዕራብ ዛሬም እንባቸውን ያፈሳሉ፤ አስቀድመው ያፈሰሱም እስካሁን እንባቸው አልደረቀም፡፡**

**በመሆኑም የሁላችንም ነጻነት ዋስትና የሚኖረው የአኙዋክ ነጻነትና መብት ሲከበር ብቻ ሳይሆን ፍትሕ፣ እኩልነትና አንድነት የሰፈነባት አዲሲቷ ስትመሰረት ብቻ እንደሆነ የሚያምነው የጋራ ንቅናቄያችን "በትዕዛዝ ፈጻሚነት" የአኙዋክን፣ የኦሮሞን፣ የአማራን፣ የኦሞ ሸለቆን፣ የኦጋዴንን፣ በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ወጣቶች በመቅጠፍ የኢትዮጵያን እናቶች እያስለቀሱ የሚገኙትን የመከላከያ ሠራዊት አባላት እየሞተ ከሚገኘው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ጎን ከመቆም ይልቅ ከሕዝብ ጋር በመቆም ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምስረታ ከብዙሃኑ ጋር እንዲሰለፉ በድጋሚ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡**

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

**************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአኢ.ጋን ሚዲያና ሕዝብግንኙነትን ግብረኃይል (**[media@solidaritymovement.org](mailto:media@solidaritymovement.org)**) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን **([www.solidaritymovement.org](http://www.solidaritymovement.org))** በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

